Oct 14, 2014

# ለጌታ የማኘት በረከት

ለጌታ ማኘት ልዩ በረከት አለው፡፡የመጀመሪያው በረከት ጌታን በሚገባ ማወቃችን ሲሆን፣ሌሎች ፍሬዎች ግን እርሱን ከማወቅ የሚመነጩናቸው፡፡
ለእግዚአብሔር የተገኘ ሰው ደግሞ ጌታን በሁሉ ነገር የበላይ ያደርጋል፣በነገሩ ሁሉ የአምላኩን ፈቃድ ያስቀድማል፣የጌታን ድምፅ ሰምቶ ይታዘዛል፣የመንግሥት ሃሳብ ይወርሰዋል እናም ሙሉ በሙሉ ትኩረቱ አምላኩ ላይ ይሆናል፡፡አዎ ለጌታ የተገኘ ሰው የራሱን አጀንዳ ይተዋና በየሄደበት ሁሉ የጌታውን ሃሳብ ያነግባል፡፡

ለጌታ ለማኘት ባጭሩ የሚከተሉትን ነው ማድረግ ያለብን፡፡ የመጀመሪያው እንዲህ ዓይነት ሰው ለመሆን ጥሩ ውሳኔና መስጠት ይፈልጋል፡፡ሁለተኛው ለሱ ልንገኝባቸው የምንችላቸውን መንገዶች ሁሉ መጠቀምን ይጨምራል፡፡ዋናዎቹም ለብቻ የምንሆንበት ጊዜ ወስኖ ቃሉን ባልተከፋፈለ ልብ ማንበብ፣ማጥናት፣ማሰላሰልና የጌታ መንፈስ ከውስጥ ወደ ውጭ እንዲለውጠን ራሳችንን በፊቱ በመጣል "እነሆኝ" ማለት ሲሆን ድምፁን ስንሰማ ደግሞ ወዲያ መታዘዝን ያካትታል፡፡

ታዲያ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ቁልፍ ተግባራዊ ነገሮች በዋናነት ጊዜን እንድንሰዋ ግድ ይሉናል፡፡ቢሆንም በዚህ ግርግርና ወከባ በበዛበት ጊዜ እግዚአብሔር ወስጣችንን እንደ ሃሳቡ በመለወጥ የፍሬ ሰዎች እንዳያደርገን ትልቁ ተግዳሮታችን ጊዜ ማጣት ነው፡፡ሞባይሉ፣ኮምፒዩተሩ፣ሶሻል ሚድያው ወዘተ ለብቻ የሚወስዱ ጊዜያትን በከባድ ተፎካካሪነት እየነጠቀን ስለሆነ፣ለውጥ አልባ፣የላይ ላይ ሰዎች እያደረገን ይገኛል፡፡እኔም የዚህ ሰለባ ስለሆንሁ አንዱ ዘወትር የምወቀስበትና የማዝንበት ጉዳይ ነው፡፡

የጽሑፍ አርዕስቴ የተወሰደበትና ሳነበው ጉጉትን የሚያሳድርብኝና የሚያስደንቀኝ ቃል መዝሙረ ዳዊት 89 ላይ ይገኛል፡፡ይህ ቃል በጸሎት ክፍለ ጊዜዬ ደጋግሜ የማነሳውና

የሚከላሰለው ቃል ሲሆን፣ አሁን ከምፅፈወም ሃሳብ ጋር ይሄዳልና ልጥቀሰው፡፡ እንዲህ ይነበባል ፡-

*"ባሪያዬን ዳዊትን አገኘሁት፣ ቅዱስ ዘይትም ቀባሁት፡፡ እጄም ትረዳዋለች፣ ክንዴም ታጸናዋለች፡፡ ጠላት በእርሱ ላይ አይጠቀምም፤ የዓመፃ ልጅም መከራ አይጨምርበትም፡፡ ጠላቶቹን ከፊቱ አጠፋለሁ፥ የሚጠሉትንም አዋርዳቸዋለሁ"* (መዝሙር 89፡ 20-23)

ይህ የተጠቀሰው ቃል ለእግዚአብሔር የመገኘትን በረከት በግልጽ ያሳየናል፡፡ ንጉሥ ዳዊት ለእግዚአብሔር ሊገኝ የቻለበት ምክንያቶች በርከት ያሉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ እንደ ልቤ የተባለ ሰወም ነበር፡፡ እኔ በበኩሌ በመዝሙሩ ወስጥ ደጋግሜ የተገነዘብሁት ነገር ንጉሥ ዳዊት በጸሎት በጌታው ፊት ወድቆ ሌት ተቀን የሚያነባ፣ በጌታው ፊት የሚጮህ፣ ለረጅም ሰዓታት የሚቃትትና ጌታውን የሚጠበቅ ሰው እንደ ነበረ አስተውያለሁ፡፡ ለአብነት ያህል፡-

*"ሁልጊዜ ከመጮኼ የተነሣ ዝም ባልሁ ጊዜ አጥንቶቼ ተበላሹ"* (መዝሙር 32:3)

*"አቤቱ ቀኑን ሁሉ ወደ አንተ እጮኻለሁና ማረኝ"* (መዝሙር 86፡ 3)

*"ይህ ችግረኛ ጮኸ እግዚአብሔርም ሰማው፣ ከመከራውም ሁሉ አዳነው"* (መዝሙር 34፡ 6)

*"አቤቱ የመድኃኒቴ አምላክ፣ በቀንና በሌሊት በፊትህ ጮኽሁ"* (መዝሙር 88፡ 1)

ከልምድ እንዳየሁት እውነተኛ በሆነ መገኘት የሚመጣ መንፈሳዊ ለወጥ ቆራጥነትን፣ ሚዛንን፣ ትኩረትን፣ መወሰንንና ያለንበትን መንፈሳዊ ሁኔታ በመንፈስ አይቶ መጥላትን ይፈልጋል፡፡ ለነገሩ ያለንበትን መንፈሳዊ ሕይወት ጌታ ዓይኖቻችንን ከፍቶ ሲያሳየን ነው ካለንበት የሚሻል ሕይወትን የምንመኘው፡፡ አለበለዚያ ከሌሎች ጋር እያስተያየን

የተሻልን ማስሎንም ልንኮፈስና ልንገበዝ እንችልም ይሆናል፡፡

በኢሳይያስ ሕይወት እንዳየነው ከምዕራፍ አንድ ጀምሮ እስከ አምስተኛው ምዕራፍ ድረስ የነበረው ትንቢት ሰዎች ላይ ያነጣጠረ ነበር፡፡ስድስተኛው ምዕራፍ ላይ ግን ጌታ በክብሩ ተገልጦ የቅድስናወን ከፍታ ሲያሳየወና እርሱ ያለበትን መንፈሳዊ ሁኔታ ሲያሳየው ነበር ደንግጦ የሚባባበት የጠፉው፡፡ከዚያማ በጌታ የተገኘ ሰው ቋንቋ ከልቡ ፈለቀ፡፡ እንዲህም ብሎ ተናገረ፡ –

*"ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ሰው በመሆኔ፣ከንፈሮቻቸውም በረከሱባቸው ሕዝብ ማካከል በመቀመጤ ዓይኖቼ የሠራዊትን ጌታ ንጉሥን እግዚአብሔርን ስለ አዩ ጠፍቻለሁና ወዮልኝ* (**Woe *is* me! for I am undone!**) *!"* (ኢሳይያስ 6፡ 5)

ለጌታ የተገኘ ሰው በነገር ሁሉ ራሱን በቅድሚያ ይመለከታል፡፡ጥሩ የንስሐ ሕይወት ይኖረዋል፡፡አምላኩን በመጁንም ከዚያ ካለበት መንፈሳዊ ሁኔታ ለመውጣትና የተሻለ ሰው ለመሆን ይቃትታል፡፡ይጮኻል፡፡የአምላኩን ጉልበት በጸሎት ይይዛል፡፡

በጌታ በመገኘት የሚመጣው በረከት ብዙ ሲሆን፣ወስጣዊ ለወጣችን ግን ቀዳሚ ነው፡፡ከዚያማ በነገር ሁሉ ጌታችንን የምናስቀድም ሰዎች እንሆናለን፡፡ቀጥሎም ምልልሳችንና አገልግሎታችን ወብትን ያገኛል፡፡ለሰዎችም ጥሩ የሚታይና የሚነበብ ምልዕክትም እንሆናለን፡፡ይህንን ሳስብ የያዕቆብ መንፈሳዊ ትግል ትዝ ይለኛል፡፡ይህም ያዕቆብ ከብዙ ወንብድናና ሚታለል በኋላ እጅ ወደ ላይ ያለበት የሚጨረሻ ትግል ነበረ፡፡ በቃኝ ያለበትና ለመገኘት የቆረጠበት እርምጃ ሲሆን "ያዕቆብም ለብቻው ቀረ" (ዘፍጥረት 32፡ 22) የሚለው ጥቅስ ቆራጥ ወሳኔወን በግልጽ ያሳየናል፡፡ አዎ ያዕቆብ ከአጠገቡ ያሉትን ሰዎች ሁሉ ለጊዜወም ቢሆን አርቆ ለብቻው ለእግዚአብሔር ተገኘ፡፡ወስዷልና፣ጨክኗልና፣ ለወጥ ፈልጓልና *"ካልባረክኸኝ አልለቅህም"* (ዘፍጥረት 32፡ 26) አለ፡፡እናም ወጤቱ አስደናቂና ከአእምሮ በላይ

ነበረ፡፡ ለእግዚአብሔር በመገኘት ያገኘውን መንፈሳዊ ለውጥ ሲናገር እንዲህ ነበር ያለው፡ -

*"እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየሁት፤ ሰውነቴም ደና ቀረች"*
(ዘፍጥረት 32፡ 30)

አንድ የእግዚአብሔር ሰው *"ዋና የቤተ ክርስትያን አገልጋዮች (በተለይ ሚድረክ ላይ የሚወጡ አገልጋዮች) ኢሳይያስ በምዕራፍ ስድስት የነበረውን ዓይነት ተመሳሳይ ልምምድ ሳይኖራቸው መድረክ ላይ መውጣት የለባቸውም"* የሚል አቋም እንዳላቸው ተናግረዋል፡፡ እኔም ይህንን ሃሳባቸውን እጋራለሁ፡፡ አዎ አገልግሎት የእሳቱ ጉጠት ከንፈሮቻችንን ካገኘው በኋላ ነው እንጂ! እኔም እንደ ያዕቆብ ዓይነት መንፈሳዊ ለውጥ ሳይኖረን ለኢየሱስ ብቁ ምስክርና አገልጋይ ልንሆን አንችልም የሚል የረጅም ጊዜ አቋም ስላለኝ በግሌ በጌታ ፊት ያለው ጸሎቴ እንደዚያ ዓይነት ለውጥ እንዲያገኘኝ ነው፡፡

ስለዚህ ወገኖቼ በተግባር ደረጃ ጌታ ጥሩ ጊዜያትን ለብቻችን ሲሰጠን ወይም እኛም ብንሆን ካለን ጊዜ ላይ ጨልፈን ቀንሰንም ቢሆን ከእግሩ ሥር በርከት ላሉ ሰዓታት መውደቅ ማስተዋል ነው እላለሁ፡፡ በዚያን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እንደሚሞላን ሆነንና የአእምሮአችንን በር ለውጫዊ ድምፆች ጠርቅመን እንደ ያዕቆብ ጌታን ፊት ለፊት እስክናየው በፊቱ እንሁን፡፡ እውነተኛ ለውጥ በውስጡ ሰውነታችን ሳይታወቀን ከወደቅንበት አንነሳ፡፡ ለምን ብትሉ እንዲህ ዓይነት ጊዜዎች ተደጋግመው ሲበዙልን ነው የመገኘታችን ዕድል ሰፊ የሚሆነው፤ መንፈሳዊ ለውጣችንም እውነተኛና የሚታይ የሚሆነው፡፡

በመጨረሻም ከላይ እንደጠቀስሁት እግዚአብሔር ፈቅዶና ሁኔታዎች ተመቻችተውልን በጸጋ ዙፋኑ ፊት ከተገኘን፤ በተግባር ደረጃ እንዲህ እናድርግ፡ -

- እግዚአብሔር እንዲነካንና እንዲለውጠን በፍቃደኝነት ልባችንን እንክፈት

- እንደ ማኅፈስ ቅዱስ ምሪት ጥልቅ ንስሐዎችን በፊቱ እንግባ
- ቢያስፈልግ የምር የሆኑ እንባዎችን በፊቱ እናፍስ
- እውነተኛ ማንነታችንን ገልጠን እናሳየው
- ድምፁን ለማስማት ሁለንተናችን እናረጋጋ
- ከጌታ እንደሚቀበል ሰው ሆነን እንጠብበቅ
- ጽኑ በሆነ ጸሎት ወደ ሚዶሪያው እንገሥግሥ
- እናም በቂና ጥራት ያለው ጊዜን በርሱ ፊት እናሳልፍ

ወገኖቼ የወሳኔ ሰዎች ሆነንና በረከቱንና ለውጥን ፈልገን በጸጋው ዙፋን ፊት ያለ ምንም ስስት ራሳችን ብንጥል ያስደንቀናል!!

በቀለ በላቸው (ዶ/ር)
beke abay@yahoo.com
240-330-5004